# በኢትዮጵያ የህዝቦችን የመብት ትግል ለውጤት ለማብቃት
# በሃገር ውስጥ ሁሉን ኣቀፍ ጠንካራ ህብረት እንዲኖር መስራት ነው

በቀለ ጅራታ

**April 24, 2017**

በኢትዮጵያ በፖለቲካ ፓርቲነት መደራጀት ከተጀመረ ከግማሽ ምእተ ኣመት በላይ ኣስቆጥሯል። መኢሶንና ኢሕኣፓ የመጀመሪያዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንደነበሩ ቢያንስ በዘመኑ የኖሩና የኢትዮጵያን ፖለቲካ ታሪክ የሚከታተሉ ሁሉ ያውቃሉ። ሁለቱም በኣንድ የጋራ ሃገር ፣ የጋራ ራእይና ህልም ላይ መተባበር ተስኗቸው በመለያየት መሳሪያ መዘው እስከ መጠፋፋት ደረሱ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ ፖለቲከኞች መካከል የመተባበር ሳይሆን የመለያየት ባህል ተዘርግቶ ይሄው እስካሁን መፍትሔ ሳያገኝ ቀጥሏል። በኣሁኑ በዘመናችን ደግሞ የመለያየ መንገዶች ባብዛኛዉ ካለፉት ታሪኮች ጋር በመቆራኘት በእጅጉ ገዝፈውና በዝተው ኣስታራቂ ሊገኝለት የማይችልበት ደረጃ ደርሶ የሃገሪቷን ህዝቦች ኖሮና የመኖር ተስፋ ኣጨልሞባቸው ይገኛል።
በጣም የሚገርመው የዘመኑ ፖለቲከኞች ባለፉት ኣርባና ሃምሳ ኣመታት ከነበሩትና ብዙም የፖለቲካ ልምድ ካልነበራቸው የዚያን ዘመኑ ትውልድ ተሽለው ባለመግኘታቸውና ከፖለቲካ ኣይዶሎጂ ልዩነት ኣልፈው በጥላቻና መናናቅ ሃገርን ወደመበታተን ጠርዝ እየገፉ መሄዳቸው ነው።በኣንድ በኩል ዛሬ ትላንት ኣለመሆኑን የማይገነዘቡና በመሬት ላይ ያለውን ተጨባጭ እውነታ ባለመቀበል ሁሉም እንደድሮ መቀጠል ኣለበት የሚሉ ወገኖች የያዙት ኣቋም ለገላጋይ ኣስቸጋሪ ሆኗል። በሌላ በኩል ደግሞ የነበሩት ኣድሎኣዊ ኣገዛዞች ያደረሱት በደሎች እንደነበሩ በመተማመን ለወደፊቱ የኢትዮጵያ ህዝቦች በእኩልነት ፣ በመከባበርና መተሳሰብ የሚኖሩባትን ፌደራላዊትና ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን በመመስረት ላይ መጀመሪያ ስምምነት ላይ ሳይደረስ ኣንድነት ሊመጣ ኣይችልም የሚሉ ወገኖች በመኖራቸው ልዩነትን ለማጥበብ በሮቹ ሁሉ ተዘግተው መቀጠላቸው ነው።
ካለፈው ታሪክ መማርና መጪውን መተንበይ የተሳናቸው ያለፉት ኣገዛዞችም ሆኑ ኣሁን የእነሱኑ ጎዳና ለማስቀጠል የሚፈልጉት እስካሁን ያልገባቸው መንገዶቹ ሁሉ ያመሩት ከጊዜ ወደ ጊዜ የሃገሪቷን ህሊውና እየተፈታተኑ እንጂ ኣንድነት፣ ሰላምና ብልጽግናን ኣላመጡም። እንዲያውም ትሻልን ትቼ ትብስን ኣገባሁ እንደሚባለው በኣንድ ሃገር ውስጥ የመኖር እድልን እንኳን እያጠበበ እንዲመጣ እያደረገ ነው። ያለፉት ኣገዛዞች ወቅቱ የሚጠይቀውን ማሻሻያዎችን ባለማድረጋቸው ያተረፉትን ወይም ያስከትሉትን መዘዞች ዶክተር መረራ ''የኢትዮጵያ የታሪክ ፈተናዎችና የሚጋጩ ህልሞች'' በሚለው መጽሃፉ ውስጥ እንደሚከተለው ኣስፍሯል።
''የንጉሱ መንግስት የኤርትራን ፌዴረሽን በማፍረስ ያገኘው ጀበሃና ሻቢያ የተባሉ ተቃዋሚዎችን ነው። በኢትዮጵያ ኣንድነት ላይ ምንም ኣይነት ጥያቄ የሌላቸውን የመጫና ቱለማ የልማት ማህበር መሪዎችን በማፈን ያገኘው ውሎ ኣድሮ የኦሮሞ ነጻ ኣውጭ ግንባር (ኦነግ) ነው። ደርግ በተራው በኢትዮጵያ ኣንድነት ላይ ምንም ጥያቄ የሌለውንና በዋናነት በትግራይ ልሂቃን የሚመራውን ኢህኣፓን በማፈን ያገኘው ሕወሐትን ነው። በዘመኑ ይሻላሉ በሚባሉ የኦሮሞ ልሂቃን ጭምር የሚመራውንና በኦሮሞ ኣካባቢዎች ሰፊ ሚና የነበረውን መኢሶንን በማፈን ያገኘው ለየት ያለ ህልም ያላቸውን የኦሮሞ ብሄርተኞችን ነው። የኢሕኣዲግ መሪዎችም ጠባብ የስልጣን ፍላጎታቸውን ለማርካት ሲሉ ሁላችንንም በእኩልነት ልታስተናግድ የምትችል ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመፍጠር የሚታገሉትን የሃገሪቷን ዲሞክራሲያዊ ሃይሎችን በማፈን የቀረችዋን ኢትዮጵያ ለበለጠ የመበታተን ኣደጋ እንዳያጋልጡ ስጋት ኣለኝ'' ሲል ከጊዜ ጋር በመራመድ ለዘመኑ የሚመጥን ፖለቲካ ለማካሄድ ዝግጁ ኣለመሆን ለዛሬው የፖለቲካ ቁርቃር መነሻ መሆኑን ኣስረድቷል። የኤርትራን ፌዴረሽን በማፍረስ ኢትዮጵያ ኤርትራንም እንዲታጣ ኣደረገ። የቆጡን ኣወርድ ብላ የብብቷን ኣጣች ኣይነት ሆነ።
ኣሁንም ቢሆን በኢትዮጵያ ኣድሎኣዊ ኣገዛዞች እንደነበሩ ያለማመንና በኢትዮጵያ ውስጥ መብታችን ኣልተከበረም የሚሉትን ወገኖች ለመስማት እንኳን ባለመፈለግ ጥያቄውን ያነሱትን ማውገዝ እያስከተለ ያለዉ ነገር ቢኖር ከመቀራረብ ይልቅ መራራቅን፣ ከፍቅር ይልቅ ጥላቻን፣ ከመተሳሰብ ይልቅ መጠራጠርን ወዘተ ብቻ ነው። ኣልፎም በምንመኘው ኣንድነት ላይ ከፍተኛ ኣደጋ እየጋረጠ ይገኛል።
ዛሬ በኢትዮጵያ ጠንካራ የፓርቲዎች ህብረት እንዳይፈጠር ካደረጉት ምክንያቶች መካከልም ልክ እንደቀድሞዎቹ ካለው ተጨባጭ የህዝቦች ፍላጎት ጋር መራመድ ያልቻሉ የፖለቲካ ሃይሎች መኖራቸው ነው።
ከላይ እንደተጠቀሰው የቀድሞዎቹ ኣገዛዞች ከጊዜው የህዝቦች ፍላጎት ጋር በመራመድ በጣም መሰረታዊ የሆኑ መብቶችን ለማስከበር የሚያስችሉ ለውጦችን ባለማድረጋቸው ዛሬ ሃገሪቷን ለገጠማት የፖለቲካ ቀውስ ዳርገዋታል። ዛሬ ላለንበት የፖለቲካ ኣሰላለፍም መንስኤዎቹ እነሱ ናቸው እንጂ የኢትዮጵያ ኣንድነት ተቆርቋሪዎች እንደሚሉት ወያኔ ወይም ኦነግ ያመጡት ኣለመሆኑን ማመን ያስፈልጋል።
ፈላጭ ቆራጩ ኣጼ ሃይለ ስላሴ ሌላው ቀርቶ ኋላ ቀሩን የጭሰኝነትና የገባር ስርዓትን እንዲያሻሽሉ በእነ ጀኔራል መንግስቱ ንዋይ

የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ከተደረገባቸው በኋላ እንኳን ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል። በኣጭሩ ንጉሱ በወቅቱ የተማሪውን የመሬት ለኣራሹ ጥያቄ እንኳን ቢመልሱ ኖሮ ምናልባት ኢትዮድያን የኣሁኑ አይነት የፖለቲካ ምስቅልቅል ባላጋጠማት ነበር። ይህ ኣሁን የተፈጠረው ሁኔታ የዛሬ ኣስተሳሰብ ያመጣው ኣለመሆኑንና ለዘመናት ሲንከባለል የመጣ ኣድሎኣዊ ኣስተዳደር መሆኑን ከዛሬ ሃምሳ ኣመታት በፊት ያንን በመቃወም የንጉሱ ከፍተኛ መኮንኖች የነበሩት እነ መቶ ኣለቃ በቀለ ሰጉና ኮሎኔል እምሩ ወንዴ የተባሉ ያሰፈሩትን ማየት በቂ ነው ። ''ኢትዮድያ የቀበሌዎቿና የህዝቦቿ ጠቅላላ ድምር ናት። ዛሬ ኢትዮድያ የሚለው ቃል ገዥውን ብቻ የሚመለከት ሆኗል። ኢትዮድያዊ ባህል ሲባል የሚነገረው የዚሁ ወገን ባህል ነው። ሃይማኖት ሲነሳ የሚነገረው ኢትዮድያ የኣንድ ሃይማኖት ተከታዮች ኣገር ሆና ነው። ስለቋንቋ ሲወሳ ኢትዮድያ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች የሚነገሩባት ኣገር መሆኗ ፈጽሞ ተክዶ ነው። የዛሬዪቱ ኢትዮድያ ህልውና የህዝቦቻችን ባህሎችና ቋንቋዎች ተደምስሰዉ ፣የገዥዉን ወገን ባህል፣ሃይማኖትና ቋንቋ እንድንወርስ ይፈለግብናልን ? ያንድ ህዝብ ውበትና ጌጡ በነዚህ ነገሮች ኣንድነት ማግኘቱ ኣይደለም። ጌጡና ውበቱ እንደምንነቱ ተከባብሮና ተቻችሎ ፣ በማይፈርስ ጽኑ ኣንድነት በነጻነት ተሳስሮ መኖሩ ነው'' ይላል።

ከላይ በመኮንኖቹ የተጠቀሱትና ከዚያም ተከትለው ይደርሱ የነበሩት በደሎች አሃዳዊው ኣገዛዝ እንዲፈርስና ለዛሬው የኣስተዳደር ኣወቃቀር ምክንያት ሆነዋል። በዚህ መሰረት በህዝቦች ማንነት ላይ የተመሰረተ የፌደራል ስርዓት ኣወቃቀር ሊመሰረት ቻለ። ይህ ኣደረጃጀት ገና በተግባር ሳይታይ ለኢትዮድያ ኣንድነት ኣስጊ ተደርጎ ከሌሎች ተቃውሞ ገጠመው። የወያኔ ቡድንም በህገ መንግስቱ ላይ ያሰፈራቸውን የዲሞክራሲ መብቶች በመጣስ እራሳቸውን በራሳቸው ያስተዳድራሉ የተባሉትን ክልሎች ከማእከል ሆኖ ለመግዛት በመፈለጉ በየክልሎቹ ህዝቦች ከፍተኛ ተቃውሞን ኣስከተለ። የወያኔ ቡድንም በዲሞክራሲያዊ መንገድ ሃገሪቱን መምራት የማይችል መሆኑን ሲረዳ ህዝቦችን የማጋጨት ተግባር ላይ ተሰማራ።ይህ ደግሞ በህዝቦች መካከል ጥላቻ፣ መፈራራትና ኣለመተማመንን ፈጠረ። የዚህ መነሻው በማንነት ላይ የተመሰረተ የፌደራል ኣወቃቀሩ ነው በማለት ቀድሞውኑ ከመነሻው የተቃወሙት ሃይሎች በሰፊው ኣራገቡት። በኣጠቃላይ የፌደራል ስርዓቱ የዜጎችን የመዘዋወር መብቶችን የሚገድብ ነው የሚለው የስርዓቱ ተቃዋሚዎች ስሞታ እያየለ መጥቶ ስርዓቱን ''የጎሳ ስርዓት'' እስከማለት ደረሱ።

ይህ ኣዲሱ የኣስተዳደር ስርዓት ለዘመናት የተጫነባቸውን የጭቆና ኣገዛዝ በማስወገድ እራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር ያስችለናል ብለው ተስፋ ያደረጉት ብሄርና ብሄረሰቦችም ምንም እንኳን ገዢዉ የወያኔ ቡድን በኢ- ዲሞክራሲያዊነቱ መብቶቻቸውን ቢገድብም በትግላቸው ያመጡትን እራስን በራስ የማስተዳደር ጅምራቸው እንዲቀለበስ የማይፈልጉ በመሆናቸው በማንነታቸው ላይ ኣንደራደርም የሚል ኣቋም እንዲይዙ ኣድርጓቸዋል። በዚህ ዓይነት የፌደራል አወቃቀሩ ሳይሆን በጭፍን የሚካሄድበት ተቃውሞ መቀጠል ሃገሪቷን ለዛሬው የፖለቲካ ቀውስ ከመዳረጉም በላይ ለኣንድነት ኣስጊ ሁኔታን ፈጥሯል።

ይህ የኣንድነት ተቆርቋሪዎች ነን በሚሉት ወገኖች የሚደረገው ተቃውሞ ጭራሹኑ ፈሩን እየለቀቀ በመሄድ በኢትዮድያ በማንነታቸው ስም የሚደራጁትን የፖለቲካ ተቃዋሚ ድርጅቶችንም የጎሳ፣ የዘር ፣ ወዘተ ድርጅቶች በማለት የማጥላላትና ኣብሮ ለመስራት ኣለመፈለገ ለሚፈልጉት ኣንድነት ተጨማሪ ስጋት እንዲፈጠር ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ ናቸው። ባለፉት 25 ኣመታትም ካለፉት ኣገዛዞች ብዙም የተለየ ኣመለካከት የሌላቸው ቡድኖች በተጫወቱትና እየተጫወቱ ባሉት ሚና የሃገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ ከድጡ ወደ ማጡ እንዲሸጋገር ኣድርጓል።

በኢትዮድያ ስም ካልሆነ በብሄር ማንነታቸው ላይ ተመስርተው የሚደራጁትን የፖለቲካ ድርጅቶችን የማይቀበሉ ወገኖች መኖራቸው በሃገር ውስጥ ጠንካራ ሃገራዊ ድርጅት እንዳይፈጠር ከፍተኛ ተጽእኖ ኣድርገዋል ቢባል ከሃቅ የራቀ ኣይሆንም። በተለይም በውጭ የሚኖሩ የኣንድነት ኣፍቃሪዎች ኣልፈውም ኣንተ ከዚህ ጋር እንጂ ከዚያኛው ፓርቲ ጋር መደራጀት የለብህም እያሉ ከመገንባት ይልቅ ሲያፈርሱ ኖረዋል።

ለዚህ ትልቁ ምሳሌ መድረክ የተባለው የፓርቲዎች ስብስብ ውይይት /ድርድር/ የተጀመረበት ጊዜና በኋም የሆነው የመለያየት ጉዳይ ነው። መድረክ በሚል መጠሪያ ውይይት የተጀመረው በስምንት የፖለቲካ ፓርቲዎች መሆኑ ይታወሳል። ፓርቲዎቹም የተሰባሰቡት ህብረብሄር ፓርቲ ነን ከሚሉትና በብሄራቸው ስም ከተደራጁት ጋር በኣንድነት እንደነበረ ይታወቃል። ውይይቱ ከኣንድ ኣመት በላይ ለፈጀ ጊዜ በመካሄድ በበርካታ ሃገራዊ ጉዳዮች ላይ ስምምነት ተደርሶ ነበር። ኣንዳንድ ህዝባዊ መሰረትና የጠራ የፖለቲካ ፕሮግራም የሌላቸው እንዲሁም ከገዢዉ ፓርቲ ጋር የውስጥ ለውስጥ ግንኙነት የነበራቸው የፓርቲ ስም የያዙ ብዙም ሳይቆዩ ከመድረክ ቢሰናበቱም ሌሎች ነጻ የሚባሉት ፓርቲዎች ኣብረው ለመቀጠል ወስነው በጋራ በርካታ እንቅስቃሴዎችን ኣድርገዋል። በነዚህ ጊዜያት ሁሉ በተለይ የውጪ ተጽእኖ ቀላል ኣልነበረም። በተለይም በኣንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ በኣጭሩ ''ኣንድነት'' ተብሎ ይጠራ በነበረው ፓርቲ ላይ ከውስጥና ከውጭ የነበረው ተጽእኖ ከፍተኛ ነበር። ለዚህም ምክንያት ኣንድነት ፓርቲ ሃገር ኣቀፍ ወይም ህብረብሄራዊ ፓርቲ ሆኖ እንዴት ከብሄር ድርጅቶች ጋር ይደራጃል የሚል ነበር። የኣንድነት ፓርቲ መሪዎች ተጽኖውን ተቋቁመው ለተወሰኑ ኣመታት የመድረክ ኣባል ሆነው ቢቆዩም እስከመጨረሻው ከመድረክ ጋር መቀጠል ኣልቻሉም።

የኣንድነት ከመድረክ መውጣት ዝግጅት የተጀመረው በምርጫ 2002 ዝግጅት ወቅት ነው። ለምርጫው ዝግጅት ማድረግ በተጀመረበት ወቅት በምርጫ ጣቢያዎች መከፋፈል ላይ ብዙ ጭቅጭቆች ተፈጥረው ነበር። ኣንድነት ልክ እንደ ''ቅንጅት'' በመላው የሃገሪቱ የምርጫ ክልሎች እወዳደራለሁ ኣለ። በሌሎች የመድረክ ኣባላት ግን ይሄ የማያስኬድና ጊዜውም ከቅንጅት ወቅት ጋር ኣንድ ስላይደለ ሁሉም ፓርቲ ገዢዉን ፓርቲ ለማሸነፍ በሚችሉበት የምርጫ ክልሎች ወይም ጣቢያዎች መወዳደር ኣለባቸው በማለት በወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ በመመርኮዝ ተከራክረዋል። ። ማሸነፍ በማንችልበት ቦታ ላይ ከተወዳደርን ለገዢዉ ፓርቲ ኣውቀን መስጠት ማለት ይሆናል በማለት በብርቱ ለማሳመን ሞክረዋል። እንደዚሁም በኦሮሚያም ሆነ በደቡብ ኣንድነት በቂ ድጋፍ ኣለው

በተባሉባቸው ከተሞች መወዳደር የሚችል መሆኑንም ጭምር በስጥቶ የመቀበል የፖለቲካ ድርድር መሰረት ሌሎች የመድረክ ኣባል ድርጅቶች ተስማምተው ነበር።

እንደሚታወቀው ’’ቅንጅት’’ በ1997 በሃገሪቱ በብዙ ቦታዎች ለማሸነፍ የቻለው ለምሳሌ በኦሮሚያ ክልል በወቅቱ የኦሮሞ ፓርቲዎች የኦሮሞ ፌደራሊስት ዲሞክራትክ ንቅናቄ (ኦፌዲን) ገና ኣዲስ የተመሰረተ በመሆኑ ህዝብ ውስጥ ዘልቆ ኣልገባም ነበር። የኦሮሞ ብሄራዊ ኮንግሬስም (ኦብኮ) በነበረበት የኣቅም ውስንነት በመላው ኦሮሚያ እጩ ለማቅረብ ኣልቻለም ነበር። ቅንጅት ደግሞ ከውጭ በሚጎርፍለት ድጋፍ በገንዘብ ፣በሰው ሃይልና ሎጂስቲክስ በጣም በተሻለ ኣቅም ላይ ስለነበር በሁሉም ክልሎች በመንቀሳቀስ ባለሁለት ጣት የምርጫ ምልክታቸውን ለማሰራጨት ችለዋል። ህዝቡም ገዢዉን ኢሕአዴግን ሙሉ በሙሉ ጠልቶት ስለነበረ ማንም ይሁን ተቃዋሚ ሆኖ ለመወዳደር የቀረበውን ለመምረጥ ወስኖ ባለሁለት ጣት ምልክት ምረጡ ተባብሎ ቅንጅትን ሊመርጥ ችሏል።

የ 2002 ምርጫ ሁኔታ ግን ከ 1997 የተለየ እንደነበር በኣንድነት ላይ ከ ውጭና ከውስጥ ተጺኖ ኣድራጊዎቹ ሊቀበሉት ኣልፈለጉም። ትላንት ዛሬ ኣይደለም የሚባለውንም ለማመን ኣልቻሉም። በ 2002 የኦሮሞ ፌደራሊስት ዲሞክራትክ ንቅናቄና (ኦፌዲን)የኦሮሞ ህዝብ ኮንግሬስ (ኦህኮ) በመላ ኦሮሚያ ኣባላትን በማፍራት ሰፊ እንቅስቃሴ ስላደረጉና ባለው የፖለቲካ ኣሰላለፍ ምክንያት ኣንድነትን የሚመርጥ እንዳልነበረ በግልጽ ይታወቃል።

በመጨረሻም ኣንድነት ከመድረክ ጋር እንዳይቀጥል ያደረገው መድረክ መዋሃድ ኣለበት የሚለው ክርክር ነበር። በመሰረቱ በህብረት ወይም በግንባር ደረጃ እንኳን ገና ብዙ ኣብረዉ ያልተጓዙና ያልተስማሙባቸው ኣቢይ ጉድዮች እያሉ የውህደት ጥያቄ ማንሳት በራሱ የማይመስልና ከመድረክ ለመውጣት ሰበብ መሆኑ ይታወቃል።በመጨረሻም መዋሃዱ ቀርቶፓርቲው እራሱ ተከፋፍሎ በኋላም ተበትኖ ቀረ። በዚህ መልክ የኣንድነት ሃይሎች ነን የሚሉትና ቡድኖች በሃገር ውስጥ ጠንካራና ገዢውን ፓርቲ የሚገዳደር ሁሉን ያቀፈ የፓርቲዎች ጥምረት ወይም ግንባር እንዳይፈጠር ትልቁን ሚና ተጫውተዋል የሚል እምነት ኣለኝ ።

እንደዚሁም እነዚሁ ወገኖች “በማንነት ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ኣደረጃጀት ዲሞክራሲያዊ ሊሆን ኣይችልም’’ የሚል ጨለምተኛ የሆነ ኣቋም በመያዝ ህብረቱ እንዳይጠናከር ኣስተዋፅኦ ኣድርገዋል። በእውነት ኢትዮጵያን ከፖለቲካ ትርምስ ለማዳንና ህዝቦችዋ ከዘመናት ድህነትና ረሃብ እንዲላቀቁ ለማድረግ ከመድረክ ኣይነት የተሻለ ኣደረጃጀት ሊኖር ኣይችልም። የመድረክ ሙሉ ስሙ “የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ኣንድነት መድረክ’’ ነው። ይህ ስም የያዛቸው ፌደራላዊ፣ ዲሞክራሲያዊና ኣንድነት የተባሉት የኢትዮጵያን የፖለቲካ ችግሮች ለመፍታት ቁልፍ ናቸው። ሁሉም እታገላለሁ የሚለው ለእነዚህ ዋና ጉዳዮች ሆኖ ሳለ በኣንድ በኩል በማንነታቸው ላይ ተመስርተው ከተቋቋሙት የብሄር ፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር መደራጀትን ’’የጎሳ ወይም የዘር ፖለቲካ ኣራማጆች’’ ናቸው እያሉ በመቀጠላቸው በርካታ ኣመታት እንደዋዛ ኣንዳችም የረባ ስራ ሳይሰራባቸው ኣልፉ። በዋናነት ግን በእነዚህ በተሳሳቱ የፖለቲካ ቁማሮች ምክንያት ለዘላለም ሰቆቃ የተዳረጉት የኢትዮጵያ ህዝቦች በሃቅ የሚታገልላቸው ጠንካራ ድርጅት እንዳይኖራቸው በማድረግ ይሄው ዛሬ ከዳር እስከዳር በሚባል ሁኔታ የጀመሩት ትግል ኣመራር በማጣት የውድ ልጆቻቸው ደም በከንቱ ፈሶ እንዲቀር ኣድርጓል።

ዶክተር መረራ “የሃገራችን ፖለቲካ የውሃ ልኩ ኣሁን ባለንበት ደረጃ የሚያዋጣው ልዩነቶችን በኣግባቡ ኣቻችሎ ሊይዝ የሚችል ጠንካራ ግንባር ብቻ ይመስለኛል’’ ያለው ኣግባብ መሆኑና ለወደፊትም ከዚህ በተለየ ሁኔታ መዳከር ለኢትዮጵያ ህዝቦች የጋራ ቤት ለመገንባት ከባድ ፈተና መሆኑን ሁሉም መረዳት ያስፈልጋል። ለኢትዮጵያ የፖለቲካ ችግሮች መፍትሔ በውጭ የተወሰኑ የፖለቲካ ቡድኖችና ድርጅቶች ለመቀራረብና ህብረት ለመፍጠር የሚያደርጉት እንቅስቃሴ የሚደገፍና ሌሎችም ልዩነትን ኣቻችሎ በጋራ በመስራቱ ያላመኑትም ቢሆኑ ምኞትና እውነታ የየቅል መሆናቸውን ተገንዝበው መከራና ሲቃይ ለሚያንገላታው ህዝባቸው ሲሉ ህብረት መፍጠሩን ቢደግፉ ለሁሉም የሚበጅ በተለይም የኣናሳው ኣገዛዝ ኣክትሞ ህዝቦች በነጻነት የሚኖሩበትን ሰላማዊ ሃገር ለመፍጠር ያስችላል ። ሆኖም በውጭ የሚኖሩ ህብረት መፍጠራቸው በሃገር ውስጥ ጠንካራ የፓርቲዎች ህብረት ወይም ግንባር እንዲኖር የሚያግዝ ካልሆነ ምንም ፋይዳ ሊኖረው ኣይችልም። በቀጥታ ከህዝቦች መካከል ሆኖ ትግላቸውን መምራት የሚችል ጥምረት ፣ ህብረት ወይም ግንባር እንበለው ከለሌ የፈለገውን ያህል ጠንካራ ግንባር ወይም ህብረት፣ ንቅናቄ በዉጭ ቢፈጠር ከሃገር ውስጡ ጋር ካልተቀናጀና ባለው ኣቅም ሁሉ ድጋፍ ካላደረገ በኣየር ላይ ሆኖ ብቻ ትግል ኣደርጋለሁ ማለት ጊዜ ከማባከን ውጪ የህዝቦችን ትግል ኣንድ እርምጃ ወደፊት መግፋት ኣይችልም።ለውጥ ማምጣት የሚቻለው በውጪ ሃገሮች ሳይሆን በሃገር ውስጥ ኣንድ ጠንካራ የፖለቲካ ህብረት መፍጠር ከተቻለ ብቻ ነው።

በውጭ ያሉ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችም በውጭ ብዙም ውጤት ለሌላቸው ስብሰባዎች ገንዘባቸውንና ጊዜያቸውን ከማባክንና ለሚነገሩት ገንቢም ሆነ ኣፍራሽ ንግግሮች በስሜታዊነት ማጨብጨብን ትተዉ በሃገር ውስጥ ሁሉን ያቀፈ ጠንካራ የፖለቲካ ፓርቲዎች ህብረት እንዲፈጠር እስካሁን መድረክን ያልተቀላቀሉት ፓርቲዎች እንዲቀላቀሉ ባላቸው ኣቅም ሁሉ መርዳትና በጎ ተጺእኖ ማድረግ ኣለባቸው ።

ምናልባት ዛሬም ’’እስካሁን በሃገር ውስጥ ሆነዉ የሚታገሉት ምንም ለውጥ ሊያመጡ ኣልቻሉም። ኢህኣዲግን በሰላማዊ ትግል ማሸነፍ ኣይቻልም በትጥቅ ካልሆነ’’ የሚሉ ሊኖሩ ይችላሉ ። እውነቱ ግን ሃገራዊ ኣጀንዳ ያለው ኣንድ ጠንካራ የፖለቲካ ህብረት ወይም ድርጅት ባለመኖሩና ህዝባዊውን የተቃውሞ ማእበል በእቅድና ወጥ በሆነ መንገድ መምራት ባለመቻሉ ነው እንጂ በሃገር ውስጥ የሚደረግ ትግል ገዢውን ፓርቲ ማንበርከክ እንደሚችል ባላፉት ሁለት ኣመታት የኦሮሞ ህዝብ ያደረገው ተጋድሎና በኋላ የጎንደርና የባህር ዳር የኣማራ ህዝብ ተጋድሎ ኣስይቷል።

በኦሮሚያ የህዝባዊ ተቃውሞ ማእበሉ ተቀጣጥሎ ገዢዉን የወያኔ ቡድን ያርበተበተዉ የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግሬስ /መድረክ

ላለፉት ቢያንስ ኣስር ኣመታት ባደረጉት ህዝብን የማንቃት ትግል መሆኑን መካድ ኣይቻልም። ስለዚህ ከኢህአዲግ ሰራሽ ውጪ ያሉት ተቃዋሚዎች ከመድረክ ጋራ ኣንድ ግንባር የፈጠሩ ቢሆን ኖሮና በሁሉም የሃገሪቷ ክልሎች በኣንድነት ትግሉን የሚመሩበትን እቅድ ቢነድፉ ኖሮ የወያኔን መንግስት ቢያንስ ለእውነተኛ ሁሉን ኣቀፍ ድርድር ማስገደድ በቻሉ ነበር። ሁሉንም ያሰባሰበና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ምኞትና ፍላጎት ኣጣምሮ የያዘ የፖለቲካ ህብረት ባለመኖሩ የህዝቦችን ትግል ለድል ለማብቃት ኣልተቻለም። በዚህም ኣምባገነኑ የወያኔ ቡድን ተጨማሪ የኣገዛዝ እድሜ እንዲኖረው ተደርጓል።

ሁሉም የፖለቲካ ቡድኖች ኣሁን ያለው ጸረ ህዝብ የሆነው ግፈኛ የወያኔ ቡድን እንዲወገድ ቢያንስ በቲዮሪ ደረጃ ይፈልጋሉ። ወደዚያ ደረጃ በሚያደርሰው መንገድ ላይ ግን ኣይደሉም። የሚካሄደው የቂም፣ የጥላቻ፣ የእልህ፣ የኣልሸነፍ ባይነት ግትር የፉክክር የፖለቲካ ትግል ነው።

እንደዚሁም ሃላፊነት በጎደላቸው ግለሰቦችና ሚዲያዎች የሚተላለፉ የፈጠራ ታሪኮች የህዝቦችን ስሜት እየኮረኮሩ መቀራረብና መንጋገር እንዳይችሉ እያደረጉ ይገኛሉ። ስለ የኢትዮጵያ ኣንድነት እየተጮሄ በሌላ በኩል ደግሞ ጸረ ኣንድነት ለሆኑ ኣስተያየቶችና ከጥላቻ ለመነጩ ልበወለድ ታሪኮች ቦታ በመስጠትና ኣልፎም የሞራል ድጋፍ የሚሰጡ ኣካላት ከዚህ ኣድራጎታቸው እስካልታቀቡ ድረስ የኢትዮጵያ ኣንድነት ምኞት ሆኖ እንደሚቀር መገንዘብ ያስፈልጋል። ኣሳዛኙ ነገር እነዚህ የታሪክ ኣዋቂ ነን የሚሉት ኣሁን ኢትዮጵያ ባለችበት የፖለቲካ ምስቅልቅል ሁኔታ ውስጥ ይህ የሚያስተላልፉት መልእክት ምን ያህል ጉዳት እንደሚያስከትል ኣለማሰባቸው ነው። ለሃገርና ለህዝቦችዋ ከታሰበ እነዚህ ሁሉ መቅረት ኣለባቸው።የኢትዮጵያ እንደ ሃገር መኖር ለሁላችንም ወሳኝ ነው። ይህንን ደግሞ ሌሎች ሊነግሩን ኣይገባም። ኢትዮጵያ የሚትዳሰስና የሚትጨበጥ ዳር ድንበር ያላት፣ የተለያዩ ባህል፣ ቋንቋና ልማድ ያላቸው ህዝቦች በየቀኑ ኣርሰው፣ ነግደውና ሰርተው የሚኖሩባት የሚትዳሰስ መሬት ናት እንጂ ''ረቂቂ፣ መንፈስ ከዚያም እንደ እግዚኣብሄር'' ናት ተብላ ሌሎች እንዲንወዳት ሊነግሩን ኣይገባም። ኢትዮጵያ የሃገር ስም ነው። ረቂቂ፣ መንፈስ ወዘተ ስለተባለች ብቻ ሊትወደድ ኣትችልም።

በኣጠቃላይ ከእንግዲህ ማንም ምድራዊ ሃይል ሊቀለብሰው የማይችለውን የፌደራል ኣወቃቀር መኮነን፣ በህዝባቸው ስም የሚደራጁትን መናቅ፣ የጎሳ፣ የዘር ፖለቲካ ብሎ ማጥላላትና ኣብሮ ለመስራት ኣለመፈለግ በምንም ኣይነት የኢትዮጵያን ኣንድነት የማያመጣ መሆኑን እየመረረም ቢሆን በመቀበል፣እውነት ለኢትዮጵያ ህዝቦች ሰላም፣ እድገትና ብልጽግና የሚያስቡ ሁሉ በሃገር ውስጥ የፓርቲዎች ህብረት ለመድረክ ድጋፍ ማድረግ ኣለባቸው። ከዚህ ውጭ የሚታሰብ ሁሉ ከንቱ ድካም ብቻ ሆኖ ይቀራል። የወያኔ ቡድንም ምንም ኣቅም ከሌላቸውና የፓርቲ ስም ከያዙት ጋር እደራደራለሁ እያለ ሲያሾፍ ሃቀኛ ተቃዋሚዎችን ማጥቃቱን ይቀጥላል። በጣም ኣስገራሚውና ለሰሚ ግራ የሚገባው ተቃዋሚዎች እራሳቸው ተደራድረው ኣንድ ህብረት ሳይኖራቸው ከገዢዉ የወያኔ ቡድን ጋር ለመደራደር መቅረባቸው ነው። ካሁን በፊት በተደረጉት ድርድሮች ሁሉ ገዢዉ ፓርቲ በኣንድ በኩል ፣ የተቃዋሚዎች ተቃዋሚ በሌላ በኩል ሆነው ነፃና ሃቀኛ ተቃዋሚዎችን ሲቃወሙ እንደነበር ይታወሳል። ዛሬም የቀጠለው ያው ነው። ተቃዋሚን ወክለው ስብሰባ ላይ ተገኝተው ተቃዋሚዎች ኣማራጭ ኣጀንዳ የላቸውም ብለው የገዢውን ቋንቋ የሚናገሩ የተቃዋሚ መሪ ነኝ የሚሉ ግለሰቦች ባሉበት የፖለቲካ ምስቅልቅል ውስጥ ከመገኘት የበለጠ ኣሳፋሪና ኣሳዛኝ ነገር ኣይኖርም።

እንግዲህ ለኣንድነት ጽኑ መሰረቱ ከላይ የጠቀስካቸው መኮንኖች እንዳሉት ያንድ ህዝብ ጌጡና ውበቱ እንደምንነቱ ተከባብሮና ተቻችሎ ፣ በማይፈርስ ጽኑ ኣንድነት በነጻነት ተሳስሮ መኖሩ ነው'' የተባለውን ልብ በማለት ኣንድነትን የሚያመጣውን ስራ ሳይሰሩ ለኣንድነት መጮህ ዋጋ የሌለው መሆኑን በመገንዘብ ከብሄር ፓርቲዎች ጋር እውነተኛ የሆነ ግንባር ለመፍጠር መዘጋጀት ያስፈልጋል። ይህ ካልሆነ ገዢው የወያኔ ኣምባገነን ቡድን ለመጪዎቹ ዘመናትም የኢትዮጵያን ህዝቦች ሙብትና ነጻነት እየረገጠ እንዲኖር ፈቃድ መስጠታችንን ማወቅ ያስፈልጋል።

ዶክተር መረራ "ፈረንጆችም ሆኑ እግዚኣብሄር የሚረዱት በሚሆን መልኩ የተደራጁትንና ጠንካራ የሆኑትን ወይም ጉልበት ያላቸውን ነው'' እንዳለው ሁሉም ከህልም ኣለም ወጥቶ በሃገር ውስጥ ከህዝቡ ጋር ሆኖ የሚታገል፣ የሚያታግል፣ የሚመራና ለድል የሚያበቃ ሁሉን ያቀፈ የፖለቲካ ፓርቲዎች ህብረት እንዲኖር መስራት ኣለባቸው። ለዚህም መድረክን ከውጭ ሆኖ ደካማ ነው ከማለት ተቀላቅሎ በማጠንከር የሚፈለገው ደረጃ ላይ ማድረስ ያስፈልጋል። በዚህም ባለፉት ታሪኮች ላይ ከመወዛገብ ኣዲስ ታሪክ በመስራት ለሁሉም የሚትሆን ኣዲሲቷን ኢትዮጵያ መገንባት ይቻላል። ።

በቀለ ጅራታ
የቀድሞው የኦፌዲን ዋና ጸሃፊ